## አጀንዳ ቁጥር 4

## የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ጥንካሬዎችና ድክመቶች መገምገም

በዚህ አጀንዳ ላይ በተደረገው ግምገማ በቅድሚያ እስካሁን ድረስ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስለራሳቸው ጥንካሬና ድክመት የነበራቸው ግንዛቤና አመለካከት ምን ይመስል እንደነበር ለመገምገም ተሞክሯል፡፡ በተደረገው ግምገማም አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች (ምንአልባትም ከኢዴአፓ-መድህን በስተቀር) በማንኛውም ዓይነት መመዘኛ እራሳቸውን ጠንካራና እንከን የለሽ አድርገው እንደሚያዩ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያለበቂ ግምገማ ገዥውን ፓርቲ ደካማ አድርገው ከመግለፅ ውጭ የራሳቸውን ጥንካሬና ድክመት በአግባቡ የመገምገም ባህሉ እስካሁን እንደሌላቸው፣ እንዲያውም እንዲህ አይነት ውስጣዊ ግምገማ እንዲደረግ የሚፈልግ ኃይል በውስጣቸው ብቅ ሲልም ጥያቄውን በቅንነት ተቀብሎ እራስን ከመገምገም ይልቅ የሠርጐ ገብነትና የአፍራሽነት ተልዕኮ አድርገው እንደሚመለከቱት፣ ይህም በራሱ ድክመታቸውን አርመው የሚጠናከሩበትን በር እንደዘጋባቸውና በየጊዜው ከውስጣቸው ለሚፈጠር ክፍፍልና አንጃኝነት ዓይነተኛ ምክኒያት እንደነበር ግምገማው አስታውሷል፡፡

ያለበቂ ግምገማና ምክኒያት ሁልጊዜ እራሳቸውን ጠንካራና እንከን የለሽ አድርጐ የመመፃደቅ ስር የሰደደ ችግር የተጠናወታቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለአለፉት 17 ዓመታት ትግላቸው ውጤታማ ሊሆን አለመቻሉ በራሱ አሳሳቢ ችግር ያለበት አቋም ላይ ስለመሆናቸው በቂ ማረጋገጫ ቢሆንም - ከምርጫ 97 በኋላ ከመዳከምም አልፎ ወደ ከፍተኛ የህልውና ፈተና ውስጥ በገቡበት ሁኔታ እንኳ እራሳቸውን በሃቅና በግልፅነት ገምግመው እንደገና ለመጠናከር የሚያስችላቸውን አቅጣጫ ለመያዝ ሲደፍሩ አይታዩም፡፡ ከገዥው ፓርቲ ጥቃት እራስን መከላከል አለመቻል ዋነኛው የድክመታቸው መገለጫ መሆኑን መገንዘብ ያልቻሉት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ዛሬም እንደ ትናንቱ ለትግል እንቅስቃሴአቸው መዳከም እህአዴግን ብቸኛ ተጠያቂ አድርጐ ማቅረብን በመምረጣቸው የ2002 ምርጫም ገዥውን ፓርቲ የበለጠ አጠናክሮ የሚያልፍበት ሁኔታ እየተመቻቸ ስለመሆኑ የሚሰማውን ስጋት ገልፆ የውይይት መድረኩ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ድክመትና ጥንካሬ እንደሚከተለው ለመገምገም ሞክሯል፡፡

ተቃዋሚው ጐራ እንደገዥው ፓርቲ ወጥ የሆነ አደረጃጀት፣ አንድ አይነት የትግል ስልትና የፖለቲካ ፕሮግራም የሌላቸው የተለያዩ ድርጅቶች በውስጡ የሚገኙበት በመሆኑ እንደ አንድ ጐራ በተወሰኑ መመዘኛዎች በበቂ ሁኔታ ሊገመገም እንደማይችል በመረዳት ግምገማው አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚጋሯቸውን ዋና ዋና ነጥቦች መሠረት በማድረግ እንዲካሄድ በቅድሚያ በመስማማት ቀደም ሲል ገዥውን ፓርቲ ለመገምገም ጥቅም ላይ በዋሉ መመዘኛዎች የተቃዋሚውን ጐራ ጥንካሬና ድክመትም በጥቅሉ እንደሚከተለው ለመገምገም ሞክሯል፡፡

ከአጠቃላይ ድርጅታዊ ሁኔታ አንፃር አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች -

1. በበቂ ሁኔታ እስከ ታችኛው የህብረተሰብ ክፍል የወረደ ድርጅታዊ መዋቅር የሌላቸው፣ ውስን ቢሮዎች፣ ውስን የፓርቲ አባላትና በቂ የገንዘብ አቅም

የሌላቸው መሆኑና ከሕዝብ ጋር ያላቸው ግንኙነት በአብዛኛው በምርጫ ወቅት ብቻ የተወሰነ መሆኑ፤

2. ጊዜውን የጠበቀ ድርጅታዊ ጠቅላላ ጉባዔ የማያካሂዱ፣ አመራራቸው በአብዛኛው በጥቂት ግለሰቦች ቁጥጥር ስር ለረዥም ጊዜ የተያዘ፣ ግልፅ የሆነ የገንዘብ አጠቃቀም ስርዓት የሌላቸውና በአብዛኛው የገንዘብ ምንጫቸው የውጭ ጥገኛ የሆነ መሆኑ፤

3. የውስጣዊ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ፣ የገዥው ፓርቲ እንቅስቃሴ፣ ውስጣዊ የድርጅታቸውንም ሆነ የአባሎቻቸውን እንቅስቃሴ በየጊዜው እየገመገሙ ከወቅትና ከሁኔታዎች ጋር የሚጣጣም አቋም የመያዝ ባህላቸው ደካማ መሆኑ፤

4. የአመራር አባሎቻቸው ከትግል ልምድ ጋር ግንኙነት በሌላቸው መስፍርቶች (በዋናነት በትምህርት ደረጃ) የሚመረጡ፣ በመካከላቸው ጠንካራ የእርስ በርስ ትስስርና መተማመን የሌላቸውና በአብዛኛውም ሕዝቡን ትክክለኛ አቅጣጫ እያመላከቱ ከመምራት ይልቅ በተቃራኒው በጊዜያዊ የሕዝብ ስሜትና ግፊት የሚመሩ መሆናቸው፤

5. በውስጣቸው የሃሣብ ወይንም የስልት ልዩነት ሲፈጠር ህገ-ደንባቸውን መሠረት ባደረገ አሠራርና የውይይት መድረክ ከመፍታት ይልቅ በአንጃኝነት፣ በስም ማጥፋትና በውጫዊ ግፊት ዴሞክራሲያዊ ባልሆነ መንገድ ችግራቸውን ይበልጥ የማባባስ ባህሪ ያላቸው መሆኑ፤

6. አብዛኛዎቹ የተቃዋሚ መሪዎች ከ1960ዎቹ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ጀምሮ በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ በነበራቸው የትግል ተሳትፎ ያሳለፉትን የጥላቻና የቂም በቀል የፖለቲካ ባህል መለወጥ ያልቻሉና በዛሬዋና በወደፊትዋ ኢትዮጵያ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን አብዛኛው ትኩረታቸው ባለፈው የትግል ሂደታቸው የእርስ በርስ ጥላቻ ላይ የተመሠረተ መሆኑ፤

7. አብዛኛዎቹ የፓርቲ አባላት የፓርቲያቸው ዝርዝር አስተሣሠብና ዓላማ በውል በመረዳት ሳይሆን በዋናነት በኢህአዴግ ተቃዋሚነትና በተለያዩ አካባቢያዊና ግላዊ ብሶቶች የተሰባሰቡ፣ ስለድርጅታቸውና ስለድርጅት አመራሮቻቸው ያላቸው እምነት በቀላል አሉባልታ የሚናድባቸው፣ ለትግሉ የሚያስፈልገውን መስዋዕትነት ሁሉ እራሳቸው በአግባቡ በመክፈል ሳይሆን የትግሉን ውጤት ከድርጅታቸው በሆነ ተዓምር የሚጠብቁ መሆናቸው፤

8. አብዛኛዎቹ ፓርቲዎች ከሕዝብ ጋር የሚገናኙበት የራሳቸው የሚዲያ አውታርና በቂ የማደራጀትና የማንቃት ስራ የሚሰሩ የሙሉ ጊዜ ሠራተኞች (ካድሬዎች) የሌላቸው መሆኑ - ከድርጅታዊ ሁኔታ አንፃር ያሉባቸው መሠረታዊ ድክመቶች እንደሆኑ በግምገማው ታምኖበታል፡፡

በየድርጅቶቹ የታቀፉ አባላት ከሌላው ህብረተሰብ በተለየ ከገዥው ፓርቲ ሊቃጣ የሚችለውን ተፅእኖ ሳይፈሩ የራሳቸውን አስተዋፅኦ ለማበርከትና ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል ተነሳሽነት ማሳየታቸው በራሱ

ሊደነቅ የሚገባውና እንደ አንድ ጥንካሬ ሊታይ የሚገባው ቢሆንም - ተቃዋሚዎች ገዥውን ፓርቲ በሕዝብ ምርጫ (አንዳንዶቹ በትጥቅ ትግል) ከሥልጣን ለማውረድ ካስቀመጡት ከባድ ዓላማ አንፃር በአሁኑ ወቅት የሚገኙበት ድርጅታዊ ሁኔታ በጣም ደካማና በብዙ ችግሮች የተሞላ እንደሆነ፣ በአጠቃላይም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ድርጅታዊ ጥንካሬ ከትግሉ ውስብስብ ባህሪና ከገዥው ፓርቲ ድርጅታዊ ጥንካሬ አንፃር ሲመዛዘን በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ (ኢዴአፓ-መድህንን ጨምሮ) አንድም ጠንካራ ሊባል የሚችል ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት አለመኖሩን ግምገማው አምኖበታል፡፡

ከአገራዊ አጀንዳዎች አንፃር የተቃዋሚውን ጐራ ለመገምገም በተደረገው ሙከራ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መንግሥታዊ ሥልጣን ያልያዙ በመሆናቸው ምክኒያት ቢያንስ በመርህ ደረጃ ከገዥው ፓርቲ በተሻለ አገርና ሕዝብ ጠቀም አጀንዳ ቀርፆ የመቅረብ እድል ያላቸው ቢሆንም አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች በዚህም ረገድ መሠረታዊ ድክመት ያለባቸው መሆኑን ግምገማው ተገንዝቧል፡፡ ከገዥው ፓርቲ ጋር ተመሳሳይ አደረጃጃት ያላቸው በብሔር ወይንም በብሔረሰብ የተደራጁ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያራምዱት የፖለቲካና የኢኮኖሚ አጀንዳ ከገዥው ፓርቲ አጀንዳዎች ብዙም የማይለዩ በመሆናቸው ገዥው ፓርቲ ላይ የሚታየው የአጀንዳ ድክመት በእነሱም ላይ እንደሚታይ፣ ይህም የሆነበት ምክኒያት ብሔርን ወይንም ብሔረሰብን መሠረት አድርጐ የተደራጀ ማንኛውም የፖለቲካ ኃይል በራሱና በሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል የሚኖረውን የኃይል ሚዛን የሚያይበት መንገድ አገራዊ አጀንዳን ከመቅረፅ አኳያ (ምክኒያታዊ ከሆነ ስጋትና ምክኒያታዊ ካልሆነ ራስ ወዳድነት የሚመነጭ) የራሱ ውስንነት ያለው በመሆኑ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡

ህብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ያላቸው አንዳንዶቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተሻለ አገርና ሕዝብ ጠቀም የሆነ አጀንዳ ያላቸው ቢሆንም አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች በዚህም ረገድ መሠረታዊ ድክመት ያለባቸው መሆኑን ግምገማው ተገንዝቧል፡፡

እነዚህ ሕብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ያላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎቻቸውን የህልውናቸው ዋና መሠረት አድርገው ከማየት ይልቅ የኢህአዴግ ተቃዋሚ መሆንን እንደ ዋና የጋራ አጀንዳ በመቁጠር በአደረጃጀት ቅርፅም ሆነ በአጀንዳ ይዘት ከማይመሳሰሉአቸው ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር አብረው መስራትን ስለሚመርጡ የያዙአቸው ጠቃሚ አጀንዳዎች “ተቃዋሚ ፓርቲ” ከሚለው ጥቅል ማንነት በላይ ጐልተው የሚታዩበት ዕድል ሲያገኙ አይታዩም፡፡ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በአማራጭነት የሚያራምዷቸውን የፖለቲካና የኢኮኖሚ አጀንዳዎች መሠረት አድርገው ገዥውን ፓርቲ በምክኒያት ከመቃወምና ከመታገል ይልቅ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ጭፍን ተቃውሞን በሥርዓቱ ላይ በማቅረብ የትግሉን የመጨረሻ ውጤት ኢህአዴግን ከሥልጣን የማስወገድ ጉዳይ ብቻ አድርገው ስለሚያቀርቡት በፖለቲካው መድረክ ላይ ግልፅና ተከታታይ የሆነ የሃሣብ ወይንም የአጀንዳ የበላይነት ሊያገኙ አልቻሉም፡፡

የተቃዋሚ ፓርቲዎች ትግል የተሻለ አማራጭ ሃሳብ በማቅረብ ሳይሆን በዋናነት ሥርዓቱን መቃወም ሆኖ በተንጠለጠለበት በአሁኑ ወቅትም የተቃዋሚዎች ደጋፊ የሆነው ሕዝብ አንዱን ተቃዋሚ ከሌላው ተቃዋሚ የሚደግፍበት ወይንም የሚነቅፍበት መመዘኛ አገራዊ አጀንዳዎችንና ስትራቴጂያዊ የትግል ስልቶችን መሠረት ያደረገ

ባለመሆኑ በደፈናው በተቃዋሚዎች ላይ "ተባበሩ ወይንም ተሠባበሩ" የሚል ተገቢ ያልሆነ ጫና እንዲፈጥር ምክኒያት ሆኗል፡፡ አብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ከሕዝብ የሚመጣን ማንኛውንም ዓይነት ጠቃሚም ሆነ ጉጂ አስተሳሰብ በፀጋ መቀበልን የዴሞክራትነት መገለጫ ወይንም ለሕዝብ ፍላጐት የመገዛት ጉዳይ አድርገው ስለሚያዩት በትግሉ ውስጥ ያላቸው ሚና የመሪነት ሳይሆን በሕዝብ ጊዜያዊ ስሜት የመመራት እንዲሆን አድርጐታል፡፡ ይህ በተቃዋሚው ጐራ ዙሪያ የሚታይ ስር የሰደደ የአስተሳሰብ ድክመትም የአገሪቱ ፖለቲካዊ ሁኔታ ከጥላቻና ከጭፍን ተቃውሞ ተላቆ የአማራጭ አጀንዳዎች (Issue politics) ትግል እንዳይሆን የራሱን አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረ ግምገማው አስምሮበታል፡፡

አብዛኛዎቹ ተቃዋሚዎች ገዥውን ፓርቲ ሁልጊዜ አምርሮ መቃወምን እንደ አንድ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት የማግኛ ስልት አድርገው በማየታቸው ምክኒያትም ብዙውን ጊዜ ከራሳቸው አጀንዳዎች ጋር የሚቃረኑና የማይጣጣሙ ትችቶች ሳይቀር በገዥው ፓርቲ ላይ ሲሰነዝሩ እንደሚታይና ይህም በራሱ ተቃዋሚዎችን ቋሚ አቋም የለሽ አድርጐ የሚያሳይ ስሜት በሂደት በሕዝቡ ውስጥ እየፈጠረ እንደመጣ፣ ይህ በጐ ያልሆነ አዝማሚያ ወደፊት ይበልጥ እየተባባሰ የሚሄድ ከሆነም ተቃዋሚዎች በመንግሥትም ሆነ በአጠቃላይ ሕዝብ (በዲፕሎማቲክ ኮሚኒቲው ጭምር) የሚኖራቸው ተቀባይነት የበለጠ እየቀጨጨ እንደሚሄድ ግምገማው አመላክቷል፡፡ ስለሆነም አንዳንድ ህብረ-ብሔራዊ አደረጃጀት ያላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች ቢያንስ በወረቀት ላይ የተሻለ አገራዊ አጀንዳ የያዙ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በአጠቃላይ ተቃዋሚው ጐራ ከዚህ መመዘኛ አንፃር ሲገመገም ግን ትግሉን የሚመራበት አቅጣጫ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎችን በዋናነት መሠረት ሊያደርግ ባለመቻሉ ምክኒያት ድርጅታዊ ሁኔታው ጠንካራ ነው ሊባሉ እንደማይችሉ ግምገማው አምኖበታል፡፡

በአጠቃላይ ተቃዋሚዎች በአሁኑ ወቅት ከድርጅታዊ ሁኔታም ሆነ ከአገራዊ አጀንዳ አኳያ ከገዥው ፓርቲ ጋር ሲነፃፀሩ በደካማ አቋም ላይ የሚገኙ መሆኑን የገመገመው መድረክ- ተቃዋሚዎች ይህንን እውነታ አምነው በመቀበል በአጭር ጊዜ ወደ ተሻለ ጥንካሬ የሚያሸጋግራቸውን ትክክለኛ አቅጣጫ ለመያዝ እስካልደፈሩ ድረስ ወደፊትም በፖለቲካ ትግሉ በኢህአዴግ ተሸናፊ ሆነው ለረዥም ጊዜ የሚቆዩበት እድል ሠፊ እንደሚሆን ያለውን ስጋት ገልፆ ግመገማውን አጠናቋል፡፡